# የትግራይ ወያኔ በሰሜን ጎንደር ዞን ምዕራብ አርማጭሆ አብደራፊ ከተማ ትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩ ተማሪዎችን በእሳት አቃጠለ።

2018/03/29

መጋቢት 19 ቀን 2010 ዓ.ም ከጥዋቱ 2:45 ሲሆን በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ዞን ምዕራብ አርማጭሆ አብደራፊ ከተማ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በክፍል በተቀመጡቀት በእሳት አቃጥለውታል ፡፡
ይህን ቃጠሎ የፈፀሙት የህወሓት አባላት ሲሆኑ እነዚህ ይህን እኩይ እና አስነዋሪ ዘግናኝ ስራ የፈፀሙት የህወሓት ደህንነቶች ሲዝቱ እንደነበር እና በአካባቢው ለሚገኙ የብአዴን ሰዎች ቢነገራቸውም ችላ በማለታቸው ይህ ድርጊት ሊፈፀም ችላል።

ቀደም ሲል የትግራይ ወያኔዎች ወልቃይት፣ ጠገዴና ተለምት ወደ ትግራይ እንዳለሉት አብደራፊን እና አካባቢውን ወደ ትግራይ ክልል ለማካለል ጥረት ቢያደርጉም የአካባቢው ህዝብ በአደረገው ከፍተኛ ተጋድሎ ሳይሳካላቸው የቀረ ቢሆንም በተደጋጋሚ ህወሓቶች ወደ አካባቢው እየመጡ ችግር ሲፈጥሩ የአካባቢው ህብረተሰብ እየሰሩት ባለው በደል በመማረር እነዚህ የህወሓት ደህንነቶች ከቦታው በራሳቸው ጊዜ ከቦታው ለቀው ከወጡ በኋላ የነዚህ የትግራይ ወያኔ የደህንነት ልጆችም ከትምርት ቤት በራሳቸው ጊዜ የለቀቁ ቢሆንም አሁንም የተለያዩ ብቀላዎችን እና በደሎችን በአብደራፊ ከተማና የአካባቢው ህዝብ ላይ እየፈጸሙ የቆዩ ቢሆንም መጋቢት 19 ቀን 2010 ዓ.ም ግን እጅግ አረመናዊ እና ዘግናኝ ስራ ነው ትምህርት ቤት በመማር ላይ በነበሩ ህፃናት እና ወጣቶች የፈፀሙት።

የትግራይ ወያኔዎች አብደራፊ ከተማ በሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት በፈጸሙት ጥቃት በአጠቃላይ በ8 ክፍሎችን ውስጥ ተማሪዎች ትምህርት በመከታተል ላይ እንዳሉ ቆልፈው በእሳት ያቃጠላቸው። በትምህርት ቤቱ ላይ በተፈጸመው በዚህ ጥቃት በረካ ተማሪዎች በእሳት የተቃተሉ ሲሆን፣ ብዙዎች ተማሪዎች ደግሞ በቃጠሎው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ተማሪዎች ሲማሩበት የነበረው ትምህርት ቤት በእሳት እየተቃጠል መሆኑ ያየው የአካባቢው ሕዝብ እና የተማሪዎቹ ወላጆች በድንጋጤ እንደመጡና በአካባዊ ከፍተኛ የጥይት ተኩስ እየተሰማ እነደነበር ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ያረጋግጣል።